

# የአያቴ ሙዞች

Ursula Nafula
Catherine Groenewald
Dawit Girma
Amharic
Level 4



የአያቴ የአትክልት ስፍራ ግሩም ነው፤ ጥራጥሬው፣ ገብሱ፣ ካዛቫው በሽበሽ ነው። ከሁሉም ሙዙ ይበልጣል። ምንም እንኳ አያቴ በርከታ የልጅ ልጆች ቢኖራትም እኔን አብልጣ እንደምትወደኝ በምስጢር አውቃለሁ። ደብቃኛለች- ሙዞችን የት እንደምታመርት። ሁልጊዜ ነው ወደቤቷ የምትጋብዘኝ። አንዳንድ ምስጢሮችንም ታወራኛለች። አንድ ምስጢር ብቻ ግን አልነገረችኝም ነበር። እሱም ሙዞቹን የት እንዲበስሉ እንዳረገች ነበር።



አንድ ቀን አንድ ትልቅ ቅርጫት ከአያቴ ቤት ውጭ ጸሐይ ላይ ተሰጥቶ ተመለከትኩ። ምን ይሆን ብዬ ሳሰላስል ‹‹ያ ምትሃተኛ ቅርጫቴ›› ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ። ከቅርጫቱ ጎን ብዙ የሙዝ ቅጠሎች ይታያሉ። በጣም በመጓጓት ‹‹አያቴ የምን ቅጠሎች ናቸው›› ብዬ ጠየኳት። ያገኘሁት ብቸኛ ምላሽም ‹‹ምትሃተኛ ቅጠሎቼ ናቸው›› የሚል ነበር።



አያቴን፣ ሙዞቹን፣ የሙዝ ቅጠሎችንና ትልቁን ቅርጫት መመልከት በጣም አስደሳች ነበር። ነገር ግን አያቴ የሆነ ነገር እንዳመጣ ወደ እናቴ ዘንድ ላከችኝ። ‹‹እባክሽ አያቴ፣ ስትሰሪ ልይ...›› ‹‹አንቺ ልጅ፣ ድርቅ አትበዪ፣ ዝም ብለሽ የተባልሽውን አድርጊ›› አለች። ወዲያው እየሮጥኩ ሄድኩ።



ስመለስ አያቴ ውጭ ተቀምጣ አገኘኋት፣ ነገር ግን ቅርጫቱም ሆነ ሙዞቹ አልነበሩም። ‹‹አያቴ፣ የታለ ቅርጫቱ፣ የታሉ ሙዞቹ ሁሉ፣ እና የታለ…›› ግን ያገኘሁት ብቸኛ ምላሽ ‹‹ከምትሃተኛው ቦታዬ ጋር ነው ያሉት›› የሚል ነበር። በጣም ነው ያስከፋኝ።



ከሁለት ቀናት በኋላ አያቴ ምርኩዟን እንዳመጣላት ወደመኝታ ቤቷ ላከችኝ። በሩን እንደከፈትኩት ወዲያውኑ ደስ የሚል አዲስ የሙዝ መዓዛ አወደኝ። ከውስጥ ደግሞ የአያቴ ምትሃተኛ ቅርጫት ነበረች። በአሮጌ ብርድልብስ በደንብ ተደብቃለች። ብድግ አረኩና ያን የሚያውድ መዓዛ በደንብ አሸተትኩት።



የአያቴ ድምጽ ከተመስጦዬ አነቃኝ። ‹‹ምን እያረሽ ነው? ቶሎ በይና ምርኩዜን አምጪልኝ››። ምርኩዟን ይዤ ቶሎ ሄድኩ። ‹‹ለምንድን ነው የምትስቂው?›› አያቴ ጠየቀችኝ። ከምትሃተኛ ቦታዋ ላይ ያለውን ድንቅ መዓዛ አሁንም ድረስ እያጣጣምኩ እንዳለሁ ጥያቄዋ አስታወሰኝ።



በሚቀጥለው ቀን አያቴ እናቴን ለመጠየቅ ስትመጣ እኔ የሙዞችን ሁኔታ ለመጨረሻ ጊዜ ለማጣራት ወደአያቴ ቤት በፍጥነት ሄድኩ። በጣም የደረሱ የሚያምሩ ሙዞች አገኘሁ። አንድ ወሰድኩና በልብሴ ደበኩ። ቅርጫቱን መልሼ ሸፈንኩና ከቤቱ ጀርባ ሄጄ ቶሎ በላሁት። በጣም ጣፋጭ ሙዝ ነበር፣ እንደዛ የሚጣፍጥ በልቼ አላውቅም።



በቀጣይ ቀን አያቴ አትክልት ስፍራው ውስጥ
ቅጠላቅጠል እየቀነጠሰች እያለ ቀስ ብዬ ተደብቄ
ወደሙዞቹ ሄድኩ። ሁሉም ለመብል ዝግጁ የሆኑ ናቸው።
በአንድ የተያያዘ አራት ሙዞችን መውሰድ አልፈለኩም።
ወደ በሩ በተረከዜ ቀስ እያልኩ ስራመድ አያቴ ስትስል
ሰማኋት። ሙዞቹን በልብሶቼ ውስጥ ደበኩና
ከበስተኋላዋ መራመድ ጀመርኩ።



ቀጣዩ ቀን የገበያ ቀን ነበር። አያቴ በጠዋት ነቅታለች። እሷ ሁልጊዜ የደረሱ ሙዞችንና ካዛቫዎችን ለመሸጥ ገበያ ትወስዳለች። በዛ ቀን ልጎበኛት ቶሎ አልሄድኩም፤ ሆኖም ከርሷ ለመራቅም አልቻልኩም።



ወደምሽት ላይ እናቴ፣ አባቴና አያቴ ጠሩኝ። ለምን እንደሆነ አወኩ። ማታ ስተኛ ከአያቴ፣ ከቤተሰቤም ሆነ ከሌላ ከማንም ሰው ላይ መስረቅ እንደሌለብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ።

# Storybooks D.C.

global-asp.github.io/storybooks-dc

## የአያቴ ሙዞች

Written by: Ursula Nafula
Illustrated by: Catherine Groenewald
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks D.C. in an effort to provide children's stories in DC's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.